# Learning by Ear 2013

## የመንታ መንገድ ትውልድ-ከባድ አማራጮችን መጋፈጥ

EPISODE THIRTEEN: **የምትወጂኝ ከሆነ አኝ**

**AUTHOR: Chrispin Mwakideu**

**EDITOR: Madelaine Meier, Yann Durand**

**COPY EDITOR: Charlotte Collins**

**List of characters by scene:**

**SCENE 1: ትዕግስት AND ምህረት IN A VAN**

- **ምህረት (F, 15)**
- **ትዕግስት (F, 15)**
- **ምኞቴ (M, 30)**

**SCENE 2: አቶ ሙላቱ SHOWS UP AT አቶ መኩሪያ OFFICE**

- **አቶ መኩሪያ (M, 55 )**
- **አቶ ሙላቱ (M, 45 )**

**SCENE 3: ምህረት, ንጉሴ AND ዳንኤል AND THE REST OF THE CLASS ON THE FOOTBALL PITCH**

- **ምህረት (F, 15 )**
- **ዳንኤል (M, 15 )**

**SCENE 4 : ወይዘሮ ዘውዲቱ IS ROBBED AT HOME**

- **MRS. ወይዘሮ ዘውዲቱ (F, 35 )**
- **ROBBER 1 (M, 20)**
- **ROBBER 2 (M, 20)**

**INTRO - NARRATOR:**

ጤና ይስጥልን ዉድ የበማድመጥ መማር ታዳሚዎች፤ ይህ "መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ" በሚል ርዕስ ከዶይቼ ቬለ ተዘጋጅቶ የሚቀርበዉ ተከታታይ ትምህርታዊ ድራማ ክፍል አስራሶስት ነዉ። ስለ ምህረት፣ ዳንኤል እና ንጉሴ የየዕለት ህይወት ታሪክ ማወቅ ትፈልጋላችሁ? እስኪ እስከዛሬ የነበረዉን ነገር መለስ ብለን እናስታዉስ ,,,

የምህረት አባት፣ አቶ ሙላቱ ፣ አዲስ የተወለደች ሴት ልጃቸውን ገንዘብ ለከፈሏቸውሀብታም ግን ደግሞ መካን ለሆኑ ባል እና ሚስት ሸጠዋል። የሸጡበትን ገንዘብ ለመጠጥ እና አዲስ ለተከራዩት ቤቱ አውለው በማለቁ ተጨማሪ ገንዘብ ለመጠየቅ ተመልሰዋል

2\. **አቶ መኩሪያ (EP 12, LINE 85)**: ሙላቱ? በዚህ ውድቅት ሌሊት ምን ታደርጋለህ? አብደህ መሆን አለበት?

3\. **አቶ ሙላቱ (LINE 97)**: “ጥሩ፣ አለቃዬ…ነገ ከፖሊሶች ጋር ትነጋገራለህ። ሴት ልጄን እንደሰረቅከኝ እነግራቸዋለሁ። **(LINE 100)** ቀላል ምርጫ ነዉ፣ መኩሪያ፤ ገንዘብ ወይስ ፖሊስ?”

አቶ መኩሪያ ይህንን ማስፈራራት ይቀበሉትው ይሆን? መልሱን ከጥቂት ጊዜ በኋላ እናረጋግጣለን። ምህረትስ? ባለፈው ጊዜ እስከ አውቶቡስ ጣቢያው ድረስ እንዲሸኛት ዳንኤልን እየጠበቀችው ነበር። ከዚያ ይልቅ ድንገት ብቅ ያለው ንጉሴ ነበርሆኖም አፍታም ሳይቆይ በድንጋጤ ነበር ክው ያለው።

**4. ምህረት (EP 12, 20):** “ንጉሴ፣ አንድ ነገር ልነግርህ እፈልጋለሁ።”

**5. ንጉሴ:** (…)“ በጆሮዎቼ፣ በልቤ፣ በሁሉም ነገሬ እሰማሻለሁ።”

**6. ምህረት:** “ንጉሴ፣ እኔ…እኔ…እንደ ሚመስለኝ…የምወደዉ……”

**7. ንጉሴ:** “እኔም እወድሻለሁ ምህረት!”

**8. ምህረት:** “ይመስለኛል ዳንኤልን እወደዋለሁ፤ አዝናለሁ ንጉሴ”

በመጨረሻ ምህረት ዉሳኔ ላይ ደርሳለች። ግን ይህን ለዳንኤል የምትነግረው መች ይሆን? ዛሬ በምናደምጠዉ “ከወደድሽኝ አሳዩኝ” በሚለዉ አስራሶስተኛ ክፍል ድራማ ታሪኩን እንከታተል፡ ፡ በመጀመርያ ወደ ትምህርት ቤት እየሄዱ ያሉትን ምህረትን እና ትዕግስትን እንከታተል።

**<u>SCENE 1: ትዕግስት AND ምህረት IN A VAN</u>**

**9. SFX: ATMO OF PEOPLE DRIVING, INSIDE A VAN WITH MUSIC IN BACKGROUND**

**10. ምህረት:** ትዕግስት ለምንድን ነው ሁል ጊዜ በአንድ አይነት መኪና የምንሄደው? በጣም ይደብራል ።

**11. ትዕግስት:** ይደብራል? በነጻ እየተጓዝሽ ይህንን የመሰለ ሙዚቃ እያደመጥሽ እንዴት ይደብራል ትያየሽ እባክሽ?

**12. ምህረት:** በነጻ ሄጄ አላውቅም! እኔ ለራሴ የመጓጓዣ ሂሳብ ሁሌም እከፍላለሁ!

**13. ትዕግስት:** በይ እሺ ይሁንልሽ በቃ! ግን ምህረት፣ ንገሪኝ እስኪ፣ ከንጉሴ ጋር ትቻችሁ ከሄድኩ በኋላ ምን ተፈጠረ?

**14. ምህረት:** **(blunt)** ምንም።

**15. ትዕግስት:**ኧረ ባክሽ…ቆይ ቆይ ግን፣ ምንም አሪፍ አጀማመር ነው። እሺ ግን ምንም ካለመከሰቱ በኋላ ፣ ቀጥሎ ምን ነበር?

**16. ምህረት:** ትዕግስት፣ ከምር ስለእዚህ ጉዳይ አሁን መናገር የምፈልግ አይመስለኝም። እንዳውም ማንንም ባላይ ደስ ። **(hesitates)** በይ የታክሲ ረዳቱ ጓደኛሽ መጣልሽ። ግን፣ እውነት ለመናገር፣ ትዕግስት፣ ትንሽ አላረጀብሽም?

**17. SFX:** ምኞቴ **APPROACHES**

**18. ምኞቴ:** **(flirting)** ኧኸ ሴቶቹ !አዲሱን አለባበሴን እንዴት አገኛችሁት አሪፍ ነዉ? አዲስ ጅንስ ሱሪ፤ አዲስ ጫማ,,,እንዳለ አዲስ ,,,ቀጥታኮ ነው ከኒዮርክ ከተማ የመጣዉ !

**19. ትዕግስት:** **(excited)** የመጨረሻ አሪፍ ነው ምኞቴ!

**20. ምኞቴ:** እሺ፣ ትዕግስት ጓደኛሽ እስከ አሁን ምንም አልተነካችም? ከጓደኛዬ ጋር ላቃጥራትላጃልሳት እችላለሁ…

**21. ምህረት:** **(surprised)** ትዕግስት፣ ምንድን ነው የሚያወራው?

**22. ትዕግስት:** **(fumbling with words)** ኧረ …ምኞቴ …አየህ …

**23. ምኞቴ:** አሃ፣ ገባኝ! አልነገርሽትም ማለት ነው፡፡ ምን ቸገረኝ-ቀረባት፡፡ እህሳ ቆንጂት-ዛሬ እንዴት ነው ትንሽ ረዘም ያለ ጉዞ አብረሽኝ ትሄጃለሽ?

**24. ትዕግስት:** **(unsure)** ግን ምኞቴ፣ የለበስኩት የትምህርት «ዩኒፎርሜን» ነው፡፡ በትምህርት ሰዓት ሰዎች መኪና ውስጥ ቢያዩኝስ...

**25. ምኞቴ:** አትጨነቂ-ለእዛ እኮ ነው ይህን የገዛሁልሽ! ቦርሳውን ክፈቺና እይ፡፡

**26. SFX: PLASTIC BAG OPENED AND CLOTHES REMOVED**

**27. ትዕግስት:** ዋው! እንዴት የሚያምር ቀሚስ ነው!

**28. ምኞቴ:** እንዴታ!-ለምታምር ልጅ ይገባታል! እና? ትመጫለሽ?

**29. ትዕግስት:** **(excited)** አዋ! አዎን፣ እመጣለሁ!

**30. ምህረት:** ትዕግስት፣ ትምህርት ሊያመልጠን አይገባም፡፡ ፈተና እየደረሰ ነው! ማጥናት አለብን፣ አለበለዚያ ልንወድቅ እንችላለን፡፡

**31. ትዕግስት:** **(unconcerned)** ላስተማሪው አሞኛል በይው፡፡

**32. ምህረት:** **(shocked)** ምን! አይሆንም፣ ትዕግስት፣ ይህንን አታድርጊ፡፡ እንዳታደርጊ...

**33. ምኞቴ:** **(cuts in)** ሰምተሻታል፡፡ እንዳመጣት ብቻ ተናገሪ፡፡ **(jokes)** ከእኔ ጋር በፍቅር ታማለች፡፡

**34. MUSIC INTERLUDE**

## SCENE TWO: አቶ ሙላቱ SHOWS UP AT አቶ መኩሪያ OFFICE

**35. SFX: ATMO INSIDE AN OFFICE**

**36. SFX: KNOCKING ON DOOR**

**37. አቶ መኩሪያ:** አቤት፣ አቶ ሙላቱ ፤ ግባ፡፡ እየጠበኩህ ነበር፡፡

**38. SFX: DOOR OPENED AND CLOSED**

**39. አቶ ሙላቱ :** የሚያምር ቢሮ አለህ፣ አቶ መኩሪያ፡፡ በጣም የሚያምር! ግን እዚያ የተጎለተችው ጸሐፊህ ጠማብኝ ነበር፡፡ ቀጠሮ የለህም ብላ ልታባርረኝ ነበር፡፡

**40. አቶ መኩሪያ:** እውነት ነው፣ ቀጠሮ አላስያዝክም፡፡ አቶ ሙላቱ ፣ ከእኔ ጋራ አደገኛ ጨዋታ እንጀመርክ አውቀኸዋል? የማይሆን አጣብቂኝ ውስጥ ገብቼ ገንዘቤን መበዝበዝ አልፈልግም፡፡

**41. አቶ ሙላቱ :** አቶ መኩሪያ፣ ምን አስጨነቀህ ገንዘብ እንደሆነ በገፍነው ያለህ፡፡ እኔ ደግሞ በጣም ትንሽ ነዉ ያለኝ ! ለትንሽ ገንዘብ ሴት ልጄን ሸጥኩልህ፡ ፡ ለአንተ እና ለቤተሰብህ ያመጣሁት ደስታ ከሰጠኸኝ ገንዘብ በጣም የሚበልጥ አይመስልህም?

**42. አቶ መኩሪያ:** (straightforward) ስማ! እኔ ነጋዴ ነኝ፡፡ በእኔ ቦታ ስምምነት ስምምነት ነው፡፡ ፣ የጅል ስራ እየሰራህ ነው ሙላቱ ፡፡ ግን ለመጨረሻ ጊዜ ነው አሁን ደግ የምሆንልህ፡፡

**43. SFX: DRAWER BEING PULLED OPENED, BANK NOTES BEING HANDED OVER**

**44. አቶ መኩሪያ:** ይኸውልህ ሌላ **20,000**። ግን አቶ ሙላቱ ፣ ላስጠንቅቅህ፤ ደግመህ ቤቴ አጠገብ ወይም ቢሮዬ አካባቢ ዝር ብትል እመነኝ፣ እንዲህ እንደማልሆንልህ እወቅ። የሚያስቸግረኝን ነገር ...ልክ የሚያስገቡልኝ ጓደኞች አሉኝ። ተረዳኸኝ?

**45. አቶ ሙላቱ :** **(excited)** በሚገባ...አዎ...ለተፈጠረው ነገር ይቅርታ፣ ጌታዬ።

**46. SFX: POCKET ZIPPER BEING OPENED**

**47. MONEY STASHED AND ZIPPER CLOSED AGAIN**

**KW BEGIN**

**48. አቶ ሙላቱ :** አመሰግናለሁ፣ የምክር ቤት አባል አቶ መኩሪያ! አሁን ወደ መንገዴ መቀጠል እችላለሁ። **(hesitates)** ግን ...ከመሄዴ በፊት...እንዴት ናት? ትንሿ ልጅ...እኔን ትመስላለች፣ ወይስ እናቷን?

**49. አቶ መኩሪያ:** **(angry)** ውጣ! ጥበቃ ጠርቼ የሰጠሁክን ከመውሰዴ በፊት ከቢሮዬ ውጣ! አንተ የማትረባ ሰካራም!

**50. አቶ ሙላቱ :** **(calmly)** እሺ፣ እሺ፣ ወጣሁ። አንድ ነገር ብቻ፤ አባክህን ሴት ልጄን ሰላም በልልኝ።

**51. አቶ መኩሪያ:** ውጣ!

**52. SFX: DOOR BEING OPENED AND CLOSED**

**KW END**

**53. MUSIC INTERLUDE**

**SCENE 3: ምህረት, እና ዳንኤል AND THE REST OF CLASS ON THE FOOTBALL PITCH**

**54. SFX: ATMO OF PUPILS OUTSIDE ON FOOTBALL FIELD**

**55. ምህረት:** (takes in deep breath) ውይ፣ ውጪ ሆኖ ፀሐይ መሞቅ እንዴት ደስ ይላል፡፡

**56. ዳንኤል:** (calls to ምህረት) ምህረት፣ ከእኔ ጋር ትንሽ ዞር ዞር ትያለለሽ? የእግር ኳስ መጫወቻው አካባቢ ደረስ ብለን እንምጣ፡፡

**57. ምህረት:** አብረን መሄድ ያለብን አይመስለኝም፣ ዳንኤል፡፡ ሰዎች ስለ እኛ ማውራት እንዲጀምሩ አልፈልግም፡፡

**58. ዳንኤል:** ምንም አይደለም፤ ርቀን አንሄድም፡፡ እባክሽን፣ አብረሽኝ ዞር ዞር በይ…

**59. ምህረት:** (sighs) እሺ፡፡

**60. SFX: FOOTSTEPS WALKING ON THE PITCH**

**61. ዳንኤል:** ምህረት፣ ክፍሉን ለምን እንደማጸዳ አውቀሻል?

**62. ምህረት:** አላወኩም፣ በፈቃደኝነት ያደረከው መሰለኝ፡፡ እናም ገርሞኝ ነበር…

**63. ዳንኤል:** (laughs out) አይደለም፣ አይደለም! ርዕሰ መምህርቷ እንደ ቅጣት እንድጠርግ አዛኝ ነው፡፡

**64. ምህረት:** (shocked) በእውነት? ምን የሚያስቀጣህ ነገርአድርገህ ነዉ?

**65. ዳንኤል:** እውነቱን ለመናገር እኔም አላወቅሁትም! ግን ...ተይው ባክሽ። ምህረት፣ አንድ ነገር ማወቅ ግን እፈልጋለሁ። እዉነቱን ንገሪኝ እኔ እንደምወድድሽ ትወድጂኛለሽ?

**KW BEGIN**

**66. ምህረት:** (nervous) ዳንኤል፣ ነገርኩህ፤ ጊዜ እፈልጋለሁ። ለምን ታስጨንቀኛለህ?

**67. ዳንኤል:** አይደለም! በእርግጥ እንደማትወጂኝ አሁን ከነገርሽኝ ደግሜ አላስቸግርሽም።

**68. ምህረት:** እያስቸገርከኝ ያለኸው በእርሱ አይደለም፣ ዳንኤል ...

**69. ዳንኤል:** ስለእዚህ ትወጂኛለሽ? ያንን ነው እያልሽኝ ያለሽው?

**70. ምህረት:** እንግዲህ...ስንነጋገር ደስ ይለኛል፣ በዛ ላይ አጠገቤ ስትሆን ጥሩ ስሜት ይሰማኛል። የሆነ መረጋጋት እና ብቻ እንደሆነ አይነት ነገር...ይሰማኛል።

**71. ዳንኤል:** በቃ? ከእዚህ የበለጠ ሌላ ነገር የለም? ሌላ ምንም አይሰማሽም፣ ልክ እንደ ጠባቂሽ (ቦዲጋርድሽ አድርገሽ ነው የምታዪኝ?

**KW END**

**72. SFX: Both stop walking**

73. ምህረት: ወይኔ ዳኒ፣ ነገሩን ዝም ብለህ እያወሳሰብክብኝ ነው።(sighs) አዎን፣ እወድድሀለሁ። ነገርኩህ አይደል እንዴ? እሺ አሁን ስለ ሌላ ነገር ማውራት እንችላለን?

74. ዳንኤል: (still not thrilled) እንግዲያዉስ አሳይኝ! ያመንሸበት አይመስልም። የምትዬው ነገር እውነት ከሆነ አሳዬኝ!

75. ምህረት: (defensive) እንዴት ማሳየት አለብኝ፣ ዳንኤል? ምን አይነት ማረጋገጫ ትፈልጋለህ?

76. ዳንኤል: በጣም አሪፍ…ድርጊት ከቃላት በላይ ይናገራል።

77. ምህረት: ድርጊት፣ ስትል ምን ማለትህ ነው?

78. ዳንኤል: (whispers) በዚህ ሳምንት መጨረሻ፣ ክፍሌ እንድትመጪ ጋብዤሻለሁ። ታድያ ብቻሽን ለመምጣት እርግጠኛ ሁኚ። ሸውጄ አስገባሻለሁ፤እሺ?

79. ምህረት: (confused) አይሆንም! ዳኒ፣ እንዴ ምን ነካህ! የምርህን ነው? እሺ ከመጣሁ በኋላስ?

KW BEGIN

80. ዳንኤል: ምህረት፣ ተረጋጊ። ጭራቅ አይደለሁም። እወድሀለሁ ብለሻል። ማንም በሌለበት ብቻችንን ሆነን እንድናወራ እፈልጋለሁ። አንድ ብቻሁለታችን!

**81. ምህረት:** አይሆንም ዳንኤል...አስፈሪ ነው። በወንዶች ማደሪያ ውስጥ አንድ ሰው ቢያገኘኝ ሁለታችንም እንባረራለን! ያንን እኔ እንደማልፈልገው ሁሉ አንተም አትፈልግም።

**82. ዳንኤል:** ግድየለሽም፣ ማንም አይባርረንም። ቃል እገባልሻለሁ።

**83. ምህረት:** ለወላጆቼ ምን እላቸዋለሁ? የሳምንት መጨረሻ፤የእረፍት ቀን ነው፤ ሁሌም እረፍት ስንሆንእናቴን እቤት ውስጥ ስራ አግዛታለሁ።

**84. ዳንኤል:** ጓደኛሽ ከተማሪዎች እኩል እንድትሆን እያገዘሻት እንደሆነ ንገሪያቸው።

**85. ምህረት:** (shocked) ወላጆቼን እንድዋሻቸው እየመከርከኝ ነው? ያንን አልችልም! ለዘለአለም አላደርገውም!

**86. ዳንኤል:** ስለእዚህ ያልሽኝ የውሸት ነው። አትወጂኝም። የምትወጂኝ ከሆነ ከእኔ ጋር ለመሆን የፈለገውን ነገር ታደርጊያለሽ። እኔም ብሆን ያንን ነዉ የማደርገው።

**87. ምህረት:** (takes deep breath) ዳንኤል፣ ለምን እንዲህ አይነት ነገር ታደርግብኛለህ? ከአንተ እና ከቤተሰቦቼ እንድመርጥ አጣብቂኝ ውስጥ ትከተኛለህ?

**88. ዳንኤል:** ላደርግ የሞከርኩት እንደ እደሱ አይደለም፣ ምህረት፤ በቅርቡ ሁላችንም ትልልቆች እንሆናለን። እራሳችንን መቻል እና በራሳችን ላይ መወሰን መጀመር ያስፈልገናል።

**89. SFX: SCHOOL BELL RINGS FROM FAR AWAY**

**90. ምህረት:** ዳንኤል፣ ይህንን ማድረግ የምችል አይመስለኝም። ፈራሁ…ወላጆቼን ትቼክአንተ ጋር፤ ይሄ ምንም ትክክለኛ ነገር አይደለም።።

**KW END**

**91. ዳንኤል:** (flatly) አጠብቅሻለሁ። ካልመጣሽ በእኔ እና በአንቺ መሀል ያለው ነገር የሚያበቃለት ይመስለኛል፣ ምህረት። አሁን ወደ ክፍል ብንገባ ይሻላል።

**92. MUSIC INTERLUDE**

**SCENE 4: MRS. ወይዘሮ ዘውዲቱ IS ROBBED AT HOME**

**93. SFX: HAIRDRYER GOES ON**

**94. ወይዘሮ ዘውዲቱ (singing a cheerful song)**

**95. SFX: HAIRDRYER GOES OFF, PERFUME BEING SPRAYED**

**96. SFX: WINDOW BEING BROKEN**

**97. TENSE MUSIC STARTS TO PLAY**

**98. ወይዘሮ ዘውዲቱ : (screams in fear)** አድኑኝ! አድኑኝ!!

**99. ROBBER 1:** ሴትዮ፣ ጸጥ በይ! ሌላ ድምጽ ብታሰሚ ጉሮሮሽን ይዤ ሲጥ አደርግሻለሁ!

**100. MRS. ወይዘሮ ዘውዲቱ : (terrified)**እሺ…እሺ….እባካችሁ፣ የምትፈልጉትን ውሰዱ ብቻ እንዳትመቱኝኝ! እንዳትጎዱኝ!

**101. ROBBER 2:** ጠፍራት እና አፏን በፕላስተር ዝጋልኝ። ከዚያም ጌጣጌጧን፣ ሞባይል ስልኳን፣ ልንይዘው የምንችለውን ኤሌክትሮኒክስ እቃ ሁሉ ሰብስብ የመኪናውንም ቁልፍ ጭምር! ጊዜ የለንም ፍጠን!

**102. SFX: MASKING TAPE BEING RIPPED, THINGS BEING HAPHAZARDLY THROWN INTO A BAG**

**103. MRS. ወይዘሮ ዘውዲቱ : (murmurs unintelligibly)**

**104. ROBBER1:** ይህ ሽቶስ አለቃ?

**105. ROBBER 2:** አትጃጃል፣ የሴት ሽቶ ነው! ሌላ ንግግር አያስፈልግም። አትለፍልፍ ስራህ ላይ አተኩር! እና ደግሞ ስሚ አንቺ- (ወደ ወይዘሮ ዘውዲቱ ) አፍሽን ዝጊ፣ ማላዘንሽን አቁሚ!

**106. MUSIC INTERLUDE**

**107. <u>OUTRO – NARRATOR:</u>**

እናም ዘራፊዎች የእነንጉሴንቤት እንዲያ ሲበረብሩ "መንታ መንገዶች ትውልድ" የተሰኘው ድራማ አስራ ሶስተኛ ክፍል ይጠቃለላል። ወደፊት ምን እንደሚከሰት ለማየት እንዲያስችለን ቀጣዩን ክፍል ድራማ አብረን እንድናደምጥ ስንል እንጋብዛለን፤ ቀጠሮአችሁ ከእኛ ጋር ይሁን፣ የዛሬዉን ድራማ በድጋሚ ማድመጥ ከፈለጉ በድረ-ገጽ አድራሻችን dw.de/lbe ላይ ያገኙታል። ድራማዉን በግል መዝገቦ ላይም ለማውረድ ይችላሉ። በፌስ ቡክ ገጻችን ላይም ሊከታተሉን እንደሚችሉ አይዘንጉ። በድጋሚ እስክንገናኝ ጤና ይስጥልን!